የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፭
አዲስ አበባ — የካቲት ፭ ቀን ፲፱፻፹፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No. 5
ADDIS ABABA – 13th February, 1996

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፲፯/፲፱፻፹፰ ዓ.ም.
ወደ ግል ይዞታ የተዛወሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለ አደራ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ............................ ገጽ ፺፱

## CONTENTS

Proclamation No. 17/1996
Establishment of the Board of Trustee for Privatized Public Enterprises Proclamation .................. Page 99

### አዋጅ ቁጥር ፲፯/፲፱፻፹፰

### ወደ ግል ይዞታ የተዛወሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለ አደራ ቦርድን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ፖሊሲ መሠረት በመንግሥት ይዞታ ሥር እንዲቆዩ ከሚደረጉት በስተቀር የልማት ድርጅቶች ወደ ግል ይዞታ የሚዛወሩ በመሆኑ ፤

በዚሁ የዝውውር ሂደት ውስጥ ወደ ግል ይዞታ የሚዛወሩ የልማት ድርጅቶችን ከሽያጭና ርክክብ በኋላ በእንጥልጥል የሚቀሩ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን ፣ እዳዎችንና ግዴታዎችን እንዲሁም የሕግ ጉዳዮችን የሚከታተልና የሚያስፈጽም አንድ የሕግ ሰውነት ያለው አካል ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ወደ ግል ይዞታ የተዛወሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለ አደራ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቍጥር ፲፯/፲፱፻፹፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· ትርጓሜ

"የልማት ድርጅት" ማለት በአዋጅ ቍጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ ወይም በተመሳሳይ ሕግ መሠረት ተቋቁሞ በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቍጥር ፹፯/፲፱፻፹፮ መሠረት ወደ ግል ይዞታ የተዛወረ የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም ቅርንጫፍ ነው።

### PROCLAMATION NO.17 /1996
### A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE BOARD OF TRUSTEE FOR PRIVATIZED PUBLIC ENTERPRISES

WHEREAS, enterprises, other than those to remain under government ownership, are to be privatized pursuant to the Economic Policy;

WHEREAS, it is found necessary to establish an organ, having legal personality, to follow-up and handle receivables, debts and obligations as well as legal cases pending after the sale and transfer of enterprises privatized in consequence thereof;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Poclamation may be cited as the "Establishment of the Board of Trustee for Privatized Public Enterprises Proclamation No. 17/1996."

2. *Definition*

"Enterprise" means a public enterprise established under Proclamation No. 25/1992 or under a similar legislation and privatized pursuant to the Ethiopian Privatization Agency Establishment Proclamation No.87/1994, or a branch thereof.

፫· መቋቋም

፩· ወደ ግል ይዞታ የተዛወሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርዱ" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል ።

፪· ቦርዱ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል ።

፬· ዋና መሥሪያ ቤት

የቦርዱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል ።

፭· ዓላማ

የቦርዱ ዓላማ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ወደ ግል ይዞታ በሚዛወሩበት ጊዜ ለአዲሱ ባለቤት የማይተላለፉ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን መሰብሰብ እዳዎችንና ግዴታዎችን መረከብ የሕግ ጉዳዮችን መከታተልና እንዲሁም እነዚህን አላማዎች እንደአስ ፈላጊነቱ በቅልጥፍና ማስፈጸም ይሆናል ።

፮· ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፤

፩· ከልማት ድርጅቱ አዲስ ባለቤት ጋር ርክክብ በሚጀመርበት ጊዜ በካዝና የሚገኘው ጥሬ ገንዘብ ተቆጥሮ በቅድሚያ ወደሚወሰን የባንክ ሂሳብ ገቢ መደረጉን ያረጋግጣል ፤ ከባንክና ከሌሎች የሂሳብ መግለጫ ሰነዶች ጋር ያገናዝባል፤

፪· በገንዘብ ሚኒስቴር አረካካቢነት ርክክብ በሚፈጸምበት ጊዜ የተገኘው ቋሚና አላቂ ንብረት ፣ ጥሬ እቃና ምርት በመዝገብ በሚታየው መጠንና ሁኔታ ለመሆኑ ዝርዝር የማገናዘብና የማስታረቅ ምርመራና ቊጥጥር እንዲካሄድ ያደርጋል ፤

፫· በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲና በልማት ድርጅቱ አዲሱ ባለቤት ወይም ሰው መካከል በተፈረመው ውል በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር ፤

ሀ) የልማት ድርጅቱ ወደግል ይዞታ እስከተዛወረበት ቀን ድረስ ሳይሰበሰቡ የቀሩ የልማት ድርጅቱን ተሰብሳቢ ሂሳቦች ይሰበስባል ፤ ለመሰብሰብ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል ፤

ለ) የልማት ድርጅቱን እዳዎች ለመንግሥት እያቀረበ እንዲከፈሉ ያደርጋል ፤ ሲፈቀድም ራሱ ይከፍላል ፤ ሌሎች ግዴታዎችን ይፈጽማል ፤

ሐ) የልማት ድርጅቱን የተሰራባቸው ሰነዶችና መዝገቦች የሠራተኞችን ፋይሎች ተረክቦ ያስቀምጣል ፤

መ) የልማት ድርጅቱን የሚመለከቱ የፍርድ ቤት ጉዳዮች በባለቤትነት ይረከባል ፤ ይከታተላል ፤ ከፍርድ ቤት ውጭ በስምምነት ይጨርሳል ፤

፬· ራሱ በሚያወጣው መርሀ-ግብርና እቅድ መሠረት ባለገንዘቦችን ይጠራል ፤ አቤቱታቸውንና ማስረጃዎችን ይቀበላል ፤ እየመረመረና እያጣራ ይወስናል ፤

፭· ወደ ግል ይዞታ የተዛወረውን የመንግሥት የልማት ድርጅት የመጨረሻ የሀብትና እዳ መግለጫ ማስታወቂያ ያወጣል ፤ የዚህን ማስታወቂያ ግልባጭ ለገንዘብ ሚኒስቴርና ለዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ያስተላልፋል ፤

፮· ስለተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳቦች እንዲሁም በፍርድ ቤት ክርክር ላይ ስለሚገኙ ጉዳዮች ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ዝርዝር ሪፖርት ያቀርባል ፤ ለኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲም በግልባጭ ያሳውቃል ፤

፯· ከሕጋዊ ሰውነቱ ጋር በተያያዘ የንብረት ባለቤት ይሆናል ፤ ውል ይዋዋላል ፤ በስሙ ይከሳል ፤ ይከሰሳል ፤

3. *Establishment*

1) There is hereby established the Board of Trustee for Privatized Public Entrprises (hereinafter "the Board") as an autonomous Public Agency having its own legal personality.

2) The Board shall be accountable to the Prime Minister.

4. *Head Office*

The Board shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as necessary.

5. *Objective*

The objective of the Board shall be to collect receivables, takeover debts and obligations and follow-up legal cases not transferred to the buyer upon privatization of a public enterprise as well as to efficiently work towards the attainment of same.

6. *Powers and Duties of the Board*

The Board shall have the following powers and duties:

1) to ensure, upon commencement of handover of an enterprise to the new owner, that all cash held at hand by the enterprise is counted and deposited in a bank account to be designated in advance, reconcile same with bank statements and other financial documents;

2) to cause inspection and supervision for item-by-item tallying and reconciliation as to whether the quantity and condition of fixed assets, stock, raw materials and finished products during handover, effected by the Ministry of Finance, corresponds with what is shown in the books of the enterprise;

3) unless otherwise provided in the contract concluded between the Ethiopian Privatization Agency and the new owner of the enterprise:

(a) to collect receivables outstanding as at the date of privatization of the enterprise, take appropriate measures for collection thereof;

(b) to submit to the government, and have settled, the debts of the enterprise, settle same itself upon approval, and discharge its other obligations;

(c) to takeover and keep the closed books and documents and the personnel files of the enterprise;

(d) to takeover and follow-up, by way of substitution, court cases relating to the enterprise, effect out-of -court settlement as appropriate;

4) to call upon creditors in accordance with its own schedule and plan, receive their claims together with supporting documents, give decision thereon after due inspection and verification;

5) to issue the final balance sheet of the privatized public enterprise, transmit copies of same to the Ministry of Finance and to the Auditor-General;

6) to submit to the Prime Minister detailed reports on receivables and payables as well as pending court cases of the enterprise, send a copy of same to the Ethiopian Privatization Agency;

7) to own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name, as attributes of its legal personality;

፰· ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል ።

፯· <u>የቦርዱ አቋም</u>

ቦርዱ ፤

፩· የሥራ አመራር ቦርድ ፤
፪· አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ እና ፤
፫· አስፈላጊው ሠራተኞች

ይኖሩታል ።

፰· <u>የሥራ አመራር ቦርድ አባላት</u>

የሥራ አመራር ቦርዱ የሚከተሉት አምስት አባላት ይኖሩታል፤

፩· በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየም ........................ ሰብሳቢ
፪· የገንዘብ ሚኒስቴር ተወካይ ................................ አባል
፫· የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ጽሕፈት ቤት ተወካይ ........................ "
፬· የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ተወካይ ....... "
፭· በቦርዱ አቅራቢነት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾም የቦርዱ ዋና ሥራ አስኪያጅ .................... አባልና ፀሐፊ

፱· <u>የሥራ አመራር ቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

የሥራ አመራር ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፤

፩· የቦርዱን ሥራዎች በበላይነት ይመራል ፡ ይቆጣጠራል ፤
፪· የልማት ድርጅቱ ወደ ግል ይዞታ እስከተዛወረበት ቀን ድረስ ሳይሰበሰቡ የቀሩ ተሰብሳቢ ሂሳቦች ገቢ መደረጋቸውን ያረጋግጣል ፤ ይቆጣጠራል ፤
፫· የልማት ድርጅቱን እዳዎች ለመክፈል ለመንግሥት አቅርቦ ያስፈቅዳል ፤ ሲፈቀድም በአግባቡ መከፈሉን ያረጋግጣል ፤ ይቆጣጠራል ፤
፬· የልማት ድርጅቱን የሚመለከቱ የሕግ ጉዳዮች በፍርድ ቤት ወይም ከፍርድ ቤት ውጭ በሚደረግ ስምምነት እልባት እንዲያገኙ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል ፤
፭· ለመንግሥት የሚቀርበውን የቦርዱን ዓመታዊ በጀትና የሥራ ፕሮግራም ያጸድቃል ፤
፮· የቦርዱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ አስፈላጊ መስሎ የሚታየውን ሁሉ ይፈጽማል ።

፲· <u>የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ተጠያቂነት</u>

፩· የሥራ አመራር ቦርዱ አባላት በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጣቸውን ተግባር በጥንቃቄ መፈጸም አለባቸው ።
፪· አባላቱ ተግባራቸውን በአግባብ ባለመፈጸማቸው ምክንያት በቦርዱ መሥሪያ ቤት ላይ ለሚደርሰው ጉዳት በአንድነትና በነጠላ ተጠያቂ ይሆናሉ ።

፲፩· <u>የሥራ አመራር ቦርዱ ስብሰባ</u>

፩· የሥራ አመራር ቦርዱ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል ።
፪· ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑ በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል ።
፫· ቦርዱ ውሳኔ የሚያሳልፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰበሳቢው ያለበት ወገን ሀሳብ የቦርዱ ውሳኔ ሆኖ ያልፋል።
፬· ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ያወጣል ።

8) carry out other activities as are necessary for the attainment of its objective.

7. *Organization of the Board*

The Board shall have:

1) a Board of Management;
2) a General Manager; and
3) the necessary staff.

8. *Members of the Board of Management*

The Board of Management shall have the following five members:

1) an Appointee of the Prime Minister ........ Chairman
2) a representative of the Ministry of Finance .................................................. member
3) a representative of the Supervising ........ Authority of Public Enterprises ............... "
4) a representative of the Ethiopian Privatization Agency ............................. "
5) the General Manager of the Board, to be appointed by the Prime Minister upon recommendation of the Board ..... member & Secretary

9. *Powers and Duties of the Board of Management*

The Board of Management shall have the following powers and duties:

1) to direct, as the superior authority, and supervise the activities of the Board;
2) to ensure and supervise the collection of receivables outstanding as at the date of privatization of the enterprise;
3) to submit to the government, and obtain approval for, the settlement of the debts of the enterprise, ensure and supervise due settlement of same upon approval;
4) to undertake proper follow-up and supervision on the settlement of legal cases relating to the enterprise in or out-of-court;
5) to approve the annual budget and work programme of the Board to be submitted to the Government;
6) to undertake whatever it deems necessary for the attainment of the objective of the Board.

10 *Liability of Members of the Board of Management*

1) Members of the Board of Management shall carry out their duties under this Proclamation with due care.
2) They shall be jointly and severally liable to the Board for damage caused to it by their failure to properly carry out their duties.

11. *Meetings of the Board of Management*

1) The Board of Management shall meet, at least, once in a month; provided that it may meet at any time, as necessary, where called upon by the Chairman.
2) There shall be a quorum where more than half of its members are present at a meeting.
3) Decisions of the Board of Management shall be made by a majority vote; in case of a tie, however, the Chairman shall have a casting vote.
4) The Board of Management shall draw-up its own rules of procedure.

፲፪. <u>የዋናው ሥራ አስኪያጁ ሥልጣንና ተግባር</u>

፩. ዋና ሥራ አስኪያጁ የሥራ አመራር ቦርዱ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የቦርዱን ሥራዎች ይመራል ያስተዳድራል ።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ሥራ አስኪያጁ ፤

ሀ) የሥራ አመራር ቦርዱ አባልና ፀሐፊ ሆኖ ይሠራል ፤

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ ለቦርዱ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሠረት የሥራ አመራር ቦርዱ የሚሰጠውን መመሪያ ያስፈጽማል ፤

ሐ) በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት የቦርዱን ሠራተኞች ይቀጥራል ፣ ያስተዳድራል ፤

መ) የቦርዱን በጀትና የሥራ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ለሥራ አመራር ቦርዱ ያቀርባል ፤

ሠ) ለቦርዱ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል ፤

ረ) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ቦርዱን ይወክላል ፤

ሰ) የቦርዱን የሥራ እንቅስቃሴና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሥራ አመራር ቦርዱ ያቀርባል ።

፫. ዋና ሥራ አስኪያጁ ለቦርዱ የሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል በሥሩ ላሉ ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፤ ሆኖም እርሱን ተክቶ የሚሰራው ኃላፊ ከ፴ ቀናት ለሚበልጥ ጊዜ የሚሰራ ከሆነ ውክልናው አስቀድሞ ለሥራ አመራር ቦርዱ ቀርቦ መፈቀድ አለበት።

፲፫. <u>በጀት</u>

የቦርዱ ዓመታዊ በጀት በፌዴራሉ መንግሥት ይመደባል ።

፲፬. <u>የመብትና ግዴታ መተላለፍ</u>

፩. በአዋጅ ቁጥር ፹፯/፲፱፻፹፮ መሠረት ወደ ግል ይዞታ የተዛወረ የመንግሥት የልማት ድርጅት ርክክቡ ሲጠናቀቅ በመንግሥት የልማት ድርጅትነት የተሰጠው የሕግ ሰውነት ይሠረዛል ። ከዚህ ጊዜም ጀምሮ የመንግሥት የልማት ድርጅትነት ሕልውናው ያበቃል ።

፪. ወደ ግል ይዞታ የተዛወረው የልማት ድርጅት እስከ መጨረሻው የርክክብ እለት ድረስ ያለው መብትና ግዴታ በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ቦርድ ይተላለፋል ።

፫. ወደ ግል ይዞታ የተዛወረው የልማት ድርጅት ርክክብ ሲጠናቀቅ ሽያጩን ሦስተኛ ወገኖች እንዲያውቁት ለማድረግ ቦርዱ ሰፊ ሥርጭት ባለው ጋዜጣ ወይም በሌላ የመገናኛ ዘዴ ሕዝቡ እንዲያውቀው ያደርጋል ።

፲፭. <u>ስለ ሂሳብ ማጣራት ሥልጣንና ተግባር</u>

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፩—፵፭ እንደ አስፈላጊነቱ ለዚህ አዋጅ ዓላማም ተፈጻሚ ይሆናሉ ። በእነዚህ አንቀጾች ስለሂሣብ ማጣራት ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ጽሕፈት ቤት የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር ወደ ግል ይዞታ የተዛወሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን በሚመለከት ለቦርዱ ተላልፏል ።

12. *Powers and Duties of the General Manager*

1) The General Manager shall, subject to the directives of the Board of Management, direct and administer the activities of the Board.

2) Without limiting the generality stated in sub-Article (1) of this Article, the General Manager shall:

(a) serve as member and secretary of the Board of Management;

(b) execute the directives of the Board of Management issued to him in accordance with the powers and duties of the Board specified under Article 6 herein;

(c) employ and administer employees of the Board in accordance with the Federal civil service laws;

(d) prepare and submit to the Board of Management the budget and work programme of the Board;

(e) effect expenditure in accordance with the approved budget and work programme of the Board;

(f) represent the Board in all its dealings with third parties;

(g) prepare and submit to the Board of Management the operational and financial reports of the Board;

3) The General Manager may delegate part of his powers and duties to subordinate officials and other employees to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Board; however, in the case of an official who acts on his behalf for more than thirty days, prior approval by the Board of Management shall be required.

13. *Budget*

The annual budget of the Board shall be allocated by the Federal Government.

14. *Transfer of Rights and Obligations*

1) The legal personality of a public enterprise, privatized pursuant to Proclamation No. 87/1994, shall be revoked upon completion of its handover to the new owner; and its existence as a Public Enterprise shall cease thereupon.

2) Rights and obligations of an enterprise as at the final date of handover shall be transferred to the Board established hereunder.

3) The Board shall publicize the privatization of an enterprise, with a view to notifying third parties of the sale, through a newspaper having wide circulation or other mass media upon completion of its handover.

15. *Power and Duty of Winding–up*

The provisions of Articles 41-45 of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992 shall apply, *mutatis mutandis,* for purposes of this Proclamation. The powers and duties of the Supervising Authority of Public Enterprises provided under these provisions, regarding the winding-up of public enterprises, are hereby transferred to the Board with respect to privatized public enterprises.

፲፮· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከየካቲት ፮ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፮ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

16 *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 13th day of February, 1996.

Done at Addis Ababa, this 13th day of February, 1996.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA